ግልፅ ደብዳቤ
ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ
ከአዲሲቷ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄ
ትርጉም መላኩ ፀጋዬ መኮንን

ህዳር 21 ቀን 2002 ዓ.ም
አድራሻ ፖስታ ሳጥን ቁጥር 1031
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ፋክስ ቁጥር 2511-55-20-20

ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ

ይህን ደብዳቤ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄ ስም ስንጽፍልዎ አገዛዘዎ የሚከተለው መርህ ብርቱ የሆነ ስጋት ስለደቀነብን ሲሆን ከበሬታችን እንደተጠበቀ ሁኖ ስለእውነት ልንጋፈጠወ ተገደድን። በአሁኑ ወቅት እርሰዎና ተባባሪ ግለሰቦች በኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ እና ብሄራዊ ጥቅም ላይ ከፍተኛ የሆነ አደጋ እንዲደቀን ምክንያት ሆናችኋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ሕዝቡን ካዱ። ሕገ መንግስቱን በመተላለፍ ህዝቡን በጭቆና አገዛዝ ቀፍድደው ያዙ። አሁን ደግሞ በእርባና ቢስ ጥቅም የወደፊት ተስፋችን እያበላሹና ብሄራዊ ጥቅምን እየሸጡ ነው። ለመሆኑ የሚኒሊክ ቤተመንግስት እና በውጭ ሀገር ባንኮች ያጠራቀሙት ገንዘብ ለእርሰዎና ለአጋሮቸው አይበቃም? አሁንም በአገዛዘወ የተራቆተውን ሕዝብ ምግብና መኖሪያ ጎጆን እየነጠቁ የምጣኔ ሀብት እድገት ብለው ይጠሩታል። ተጨባጩ እውነታው ግን በእርሰወ መሪነት በተደራጁ እና ባልተመረጡ በህገ ወጥ ወንጀለኞች የሚካሄድ መጠነ ሰፊ ዘረፋ ነው። እንዲህ አይነት ጥቅም ያለው ምን ጊዜም አይጠግብም። የሞራል ህግ በእርሰወ ዘንድ አይታሰብም፣ እውነት ውሸት ሁኖ ነው የመቆጠረው የእርሰወ እውነት ውሸት ብቻ ነው። በዚህ አሰራር ከቀጠሉ የኢትዮጵያ ውድቀት የማይቀር ደረጃ እየገፉት ነው።

ድሮ ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት አልወደቀችም ነበር። አሁን ግን እርሰወ የሚፈልጉትን ለማሳካት ሲሉ ሀገሪቱን "በእርሰወ መንግስት ባርነት ስር ወደቀች" በዚህ ህገወጥ አሰራረወ ለመቋቋም የሞከሩ ሁሉ ይጉላላሉ፣ ይገረፋሉ ፣ይታሰራሉ ወይም ይገደላሉ።ህወሀት በሚቆጣጠረው "የህግ አገዛዝ" ብሎ በሚጠራው በህግ ስም ተቀባይነት የሌለው ተግባር ይፈጽማሉ። በርካታ ቆራጥ፣ ብርቱ፣ ትሁትና ታማኝ ኢትዮጵያዊያን ብርቱካን ሚዴቅሳንና በሽህዎች የሚቆጠሩትን ጨምሮ የግፍ አሰራርን በመቋቋማቸው ወይም ይቋቋሙኛል በሚል ስጋት ብቻ በሀሰተኛ ክስ ሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ እስር ቤቶችና ማጎሪያ ማእከላት ይጉላላሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ!

እርሰወ ኑሮ ከብዶት ኑሮውን ለማሸነፍ ለሚጣጣረው በሚሊዮን ለሚቆጠረው ሕዝብ የሚሰጡት ትኩረት በጣም የኮሰመነ ነው። መሬታቸውና መብታቸውን ሲቀሙአቸው የእርሰወን እርምጃ ለመቋቋም የሚያስችል አቅም በሌላቸውና አንዳዶች በርትተው ሲቋቋሙ ወይም ሲዋጉ አሸባሪ የሚል ስም ይለጥፉባቸዋል፡ በመቀጠልም ህወሀት የሚቆጣጠረውን እገሌ ከገሌ ሳይል ሁሉንም በመደዳ ከነብሄረሰባቸው ቅጣት የሚሰጥ ርህራሄ ቢስ ወታደራዊ ሰራዊት ያዘምቱባቸዋል። በብሄራዊ ጦር ውስጥ የዘር ማጥፋትና በሰብአዊ ፍጡር ላይ ግፍ የመፈጸሙ የጦር ወንጀሎችን መንግሥተወ ከለላ ሁኖአል። በተመሳሳይ ሁኔታ በውትድርና ሙያ የተሰማሩ ብዙ ጥሩ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ወደ አልፈለጉት ጦርነት በእነዚህ የጦር ግፍ በፈጸሙ ወታደሮች መሪነት እየተገፉ በሶማሊያ ብሎም በራሳችን ህዝብ በኦጋዴን፣ በጋምቤላ፣ በኦሮሚያና በመላ ሀገሪቱ ይህንኑ እንዲፈጽሙ ተገደዋል። አገዛዝወ የሕዝቡን የደህንነት ዋስትና መጠበቅ ሲገባው በተቃራኒው የሕዝቡን ዋስትና ይገፋል፣ ያርቃል።

የምንለው ነገር ቢኖር ፈጣሪ በእርሰወ ሰይጣናዊ አገዛዝ እጅ የወደቀውን ሕዝብ ፍቅሩን ብቻ ሳይሆን ጥንካሬውንና ምህረቱን እንዲያወርድ እንለምናለን። የእርሰወ ዘመን ሲያከትምና እውነተኛው ቀን ሲደርስ ወደ ጥፋት ከሚያመራ ተግባር እንዲታቃብ በአምላክ የሞራል ሕግና በሰብአዊነት ላይ የተመሰረተ ጥበቃ ስር እንደሚያሳርፈውም እምነታችን የጸና ነው። ይህ የለውጥ ጊዜ በፍጥነት እየገሰገሰ ነው። ለምን ቢሊ በእርሰወ አገዛዝ ኢትዮጵያ በቃት! በአብሔር ዘንድ የማይቻል ነገር የለም፣ ጌታ ደግሞ መማለጃ አይሻም።

ምን ጉድ ነው? የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደበርበሬ የሚያቃጥል፣ እንደሚጥሚጣ የሚለበልብ፣ በሕዝብ ላይ በጥላቻ በተመረዘ ስሜት፣ ጨካኝ፣ለጥቅም ሲል የሚሰጠው ውሳኔ የተዛባ፣ የተጭበረበረና በአድለወ ላይ የተመሰረተ ሀገሪቱን የሚጠላ መሪ ላይ የጣለው። እናውቃለን ለተንኮል ስራ በጣም መሀንዲሱ እንደሆኑ ይህ ለእርሰወ ካልሆነ ለማንም ጎጂ ነው። የእርሰወን አላማ በውል ላልተረዱ ብዙወች ከስልጣን እንደተፈናጠጡ ለምን ኤርትራ እንድትገነጠልና ኢትዮጵያን ያለባህር በር እንዳስቀሩ በወቅቱ ብዙም ግንዛቤ አልነበረም። ሳይዘገይ ግን የፖለቲካውን ቀመር ቀድመው የተገነዘቡት ሪፖርተሮች የእርሰወ አላማ ብቸኛ የኢትዮጵያ የበላይ ግኘ የመሆን ፍላጎት ላይ ያተኮረ መሆኑን ይፋ እስከሚያደርጉት ድረስ ።

አቶ ጠቅላይ ሚኒስትር!

አሁንም ይህንኑ እየደገሙት ነው።በደመ ነብስ የሚነዳው አገዛዘወ (እርሰወን) የሚተካ መሰል አሻጉሊት ሳይጎልቱበት ከእጀወ እያመለጠ እና እየተቀደሙ መሆኑን ያነፈነፉት ይመስለናል። በመሆኑም የሕዝቡን ጬኸት ባለመስማት የራሰወትን ተጭማሪ ሀብት ለማግበስበስ ብሄራዊ ሀብቱን ለገበያ ድርድር አቅርበውታል። ይህም በምዝበራና ብኩንነት ለነቀዘው አገዛዘወ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ሲሉ ለመሸጡ ብቸኛው አመች ስርአትና የእነርሱ ፍላጎት ፈጻሚ መሆነወትን ለማሳየት እና የእነርሱን ድጋፍ ለመሸመት የሚያደርጉት ተግባር ነው።የእርሰወ ያልሆነውን በመሸጥ ግን የሚያተርፉት ነገር ቢኖር የኢትዮጵያዊያንን ብስጭትና ቁጭት ይበልጥ በማቀጣጠል በአገዛዘወ ላይ ተጨማሪ ህዝባዊ መነሳሳት ምክንያት መሆን ነው። በአንድ ላይ አብረው ይህንን ጸረ ብሄራዊ ተንኮል ሊያስቆሙ ተዘጋጅተዋል።እርሰወ በስም ብቻ ነው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚባሉት። ምክንያቱም አልተመረጡም፣ለሕዝቡና ለሕገመንግስቱ ያለበወትን ሀላፊነት አልተወጡም። የሕግ የበላይነት ባለበት ሀገር ቢሆን ኑሮ የሀገር ክህደት ወንጀል በመፈጸም ተፈርዶብወ ዘብጥያ መውረድ በተገባወ ነበር።

አቶ ጠቅላይ ሚኒስትር!

የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት በአለም በአመቱ 5ኛ ፈጣን እድገት ያስመዘገቡ ተብሎ እንዲሞካሽ የማስመሰያና የሀሰተኛ እቅድና ቁጥር የሚመግቧቸው አሽቃባጮችን በመጠቀም የህዝቡን አስተሳሰብ ለመሳብ አይሞክሩ። የሚያሳዝነው እውነቱ ግን በእርሰወ የተመራው የዘረፋና የቅሚያ ቡድን የምትጠቀሙበት ስልት እንዴት እንደሆነ አለመጠየቃቸው ነው? ለመሆኑ የኢትዮጵያን የዘይት፣ የነዳጅ፣ የወርቅ፣ የውሀ፣ የደን፣ የእርሻ መሬት፣ ንጥር ነገሮች /ሚኒራልስ/፣"የንግድ ተጠቃሚነትን መብት ለባእዳን አለማቀፍ ጥቅም ፈላጊዎች፣ ለቤተሰበወ፣ ለህወሀት መሪዎች፣ ለግል ደጋፊወችና ለውጭ መንግስታት፣ ብሎም ለባእዳን የንግድ ድርጅቶች ጥሩ አጋጣሚ "ጥሩ የመበዝበዣ" ዘዴ ለሚሹ ከዚህ በተጨማሪ የሀገር ውስጡን ችግር ያልተረዱ አንዳንድ እውነተኛ ሽሪኮች የእርሰወን ጨካኝነት፣ ኢሰብአዊነት፣ በሚስጢር የማይደግፉትን የሚያጠፉና የሕዝቡን ፈቃድ የጣሱ ሰው መሆነወን ያልተገነዘቡ ናቸው። የምጣኔ ሀብት ጠበብቱ ዘገባ እርሰወ በሕዝቡ ጭቅላት ላይ አፈሙዝ ደቅነው እየፈጸሙ ያለውን ሞራለቢስ በሆነ መንፈስ ለእርሰወና አጋሮች ሀገሪቱን እየዘረፉ ስለአለው ሁኔታ መረጃ ማቅረብ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር!

እየሸጡ ያለውን ቦታ "ጥቅም ላይ ያልዋለ" "ሰው ያልደረሰበት" ነው ይላሉ።ይህ ግን ፈጽሞ ውሸት ነው።በጤነኛ እምሮ ያሉ ኢትዮጵያዊያን በሚገባ ያውቁታል። የሚያደርጉት ተግባር ግን መሬት ማራቆትና አቅመ ደካማና መከላከል የማይችሉ ለዘመናት በአካባቢው የሚኖሩትን ተወላጆች ማፈናቀል ነው። አካባቢው እንኳን በኢትዮጵያዊያን ይቅርና በአለማቀፍ ሕብረተሰብ ሳይቀር የታወቁ ዜጎች የሚኖሩበት ነው። እርሰወና አገዛዘወ እንድታውቁት የሚገባው የሚያካሂዱት ተግባር የአካባቢ ተወላጆች መሬት እንዲጠበቅ የሚለውን አለማቀፍ ሕግ የጣሰ መሆኑን ነው። በተጨማሪ ማን ነው የኢትዮጵያን ግዛት ለሱዳን አሳልፈው እንዲሰጡ መብት የሰጠወት? ይህ የኢትዮጵያዊያን ይዞታ ነው። በኢትዮጵያና በሱዳን መካከል የደንበር ወሰን ማደረግ አያስፈልግም። ወሰኑ ከመቶ አመት በፊት ስምምነት የተደረገበት ጉዳይ ነው። በምን መሰረት ነው የኢትዮጵያን ብሔራዊ ደህንነት የሚጥሱት? ለውጭ ሰዎች ማንም አልያዘውም በሚል ለ35 አመት መሬታቸውን በሊዝ/ውል/ እየሰጡ ያሉት? በስልታዊ አገላለጽ ማንም አይጠቀምበትም፡ ምክንያቱ ግን አገዛዘወ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መርህ አራማጅ በመሆኑ መሬቱን በባለቤትነት ህዝቡ እንዳይጠቀምበት በመከልከሉ የተነሳ ነው።

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሰው ያልደረሰበትና በግል ያልተያዘ መሬት የለም።በተጨማሪ አለማቀፍ ጠበብት እንደሚተነብዩት በሚቀጥሉት ወራት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ለረሀብና ለቸነፈር ይዳረጋሉ። በቁጥሩ ላይ ለመቀነስ ይፍጨረጨራሉ አለያም "በድርቅ" ያመካኛሉ። ምርታማ የሆነ ለም መሬትና የውሃ ሀብት መኖሩን በየትም ቦታ ያስተዋውቃሉ፣ በተቃራኒው እርሰወ የልመና ኮፋዳወትን ይዘው ለምግብ እርዳታ አለማቀፉን ህብረተሰብ ከመቅረበወ በፊት ለምንድን ነው እነዚህ ቦታወች በኢትዮጵያዊያን የማይያዙትና በሚሊዮን ለሚቆጠሩት ችግረኛ ወገኖቻችን ችግር መፍቻ መፍትሄ የማይፈለገው?

አሁን ሕዝቡ ምንም መብትም ድምፅም የለውም። ነገር ግን በሂደት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ተነስቶ በስማችን እንደዚህ አይነት የመደራደር ወይም በሌሎች ንብረት ላይ ትርፍ የማግኘት መብት የለወትም ማለቱ አይቀሬ ነው። ይህ መንግስት ሲወድቅ በእርሰወ የተደረገው ህገወጥ ውል ብሎም ብሄራዊ ጥቅምን የሚነካ ውል ሁሉ ፋርሽ ይሆናል። ማንም በዚህ ስርአት የለሽ ሂደት ለመጠቀም ነጻነት በጎደለው የሕግ የበላይነት በሌለበትና የሕዝብን ፍላጎት በጨፈለቀ መልኩ የሚዋዋሉ ሁሉ ውድቅ እንደሚሆን ሊገነዘቡና ሊያውቁት ይገባል።

አቶ ጠቅላይ ሚኒስትር!

የኢትዮጵያዊያንን ኑሮና የወደፊት እድል ያለጠባቂ አስቀሩት።አሁን በቀጥታ ልንነግረወ እንፈልጋለን፤

አንደኛ፡ እንዲህ አይነት ውል ለመዋዋል መብት የለወትም፣ የ1997ን ጨምሮ ያለፉትን ምርጫወች አጭበርብረዋል፣እራሰወትን አሸናፊ ብለው አውጀዋል፣በርካታ ሰወችን በአሰቃቂ ሁኔታ ገለዋል፣ 197 ሰላማዊ ሰወችን በጥይት አስረሽነዋል፣በአስር ሺወች የሚቆጠሩ አፍሰው አስረዋል፣ገርፈዋል፣የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት መሪዎችን ለ20 ወራት አስረዋል፣197 ሰዎች መገደል በእነሱ አመካኝተዋል እውነታው ግን እርሰወና አገዛዘወ ነው ለዚህ ወንጀል ተጠያቂው ለማጠቃለል ህገ ወጥ መሪ ነወ።

በሁለተኛ፡ ሕገ መንግስቱን ጣሱ፣ ሕዝቡን ጨቆኑ በሌላ በኩል እራስወትን በቡድን 20 የአፍሪካ ወኪል ለመሆን እራሰወትን አዘጋጁ አሁን ደግሞ ኮፐንሀገን በሚካሄደው የከባቢ አየር የመሪወች ስብሰባ አፍሪካን ወክለው ለመገኘት በሂደት ላይ ነወት፣ይጠብቁ በፈጸሙት የሰብአዊ መብት ወንጀል የብዙሀን መገናኛ ትኩረት የሚስብ መሆኑ። ባለፈው የለንደን ቡድን 20 ሊያካሂዱ የነ በረውን ጋዜጣዊ መግለጫ በመጨረሻው ደቂቃ እንዲሰርዙ የተገደዱበት ሁኔታ አሁንም ይደገማል። ይኸውም የጋዜጠኞችን ጥያቄ መጋፈጥ ውሸተወን፣ ማታለልወን፣በህዝቡ መካከል የሚፈጽሙትን ሸብር፣ሀገሪቱን በአፈሙዝ ስር ማድረገወን እንዳይጋለጡ ከእውነት ሸሹ። ይህንን ከመጋፈጥ ይልቅ መላ አህጉሩን ባሳፈረ መልኩ መግለጫውን ሰረዙ እውን ኢትዮጵያም ሆነ አፍሪካ እንዲህ አይነት ጋዜጠኞችን የሚፈራ ተወካይ ይሻሉን? አወ በጣም ብልጣብልጥ ነወ "ስርአቱን አውቀውታል" እንዴት ገንዘብ ከምራባዊያን እንደሚገኝ ነገር ግን ያለፈው የውርደት ስራወ በአፍሪካ ጋር ሊጣጣም አይችል ይሆናል።

ሆኖም ስለ አካባቢ አየር የሚያደርጉት ዘመቻ ጋዜጠኖች ስለ ራሰወ የአካባቢ አየር ይዞታ የማይጠይቀወት ይመስለወታል።እስኪ ትንሽ ምሳሌወችን እንወሰድ በኦሮሚያ ቆቃን ተመልከቱ በአፋር ክልል የአዋሽን ወንዝ ወይንም የአቃቂን ወንዝ ሲወርድ ቀይና ሰማያዊ መልክ ይዞ፣ኢትዮጵያዊያን ንጹህ የመጠጥ ውሃ ከማያገኙት የአለም ሕዝቦች ከቀዳሚዎቹ መካከል ናቸው።አሁን ደግሞ አንዳንድ የመርህ ስርአትን የማይከተሉ የውጭ ድርጅቶች በሃገራቸው በአደገኛ መርዝነታቸውና አካባቢን በማበላሸት የተከለከሉትን ኬሚካል በእኛ ሀገር በመጠቀም ወንዞቹን ለተጨማሪ ብክለት እየዳረጉ ነው። በተጨማሪ መጠነ ሰፊ የተፈጥሮ ደኖች ባለፉት አመታት ተጨፍጭፈዋል። አሁን ደግሞ እነዚህ የውጭ ሀገራትና ኩባንያወች ተጨማሪ የደን ምንጠራ በተለገሳቸው የመሬት ይዞታ ላይ ያካሂዳሉ። ይህን እያደረጉ ለምንድን ነው ምራቡን ተጠያቂ የሚያደርጉት።

አቶ ጠቅላይ ሚኒስትር!

እኛ የምንለውን በተሳሳተ መንገድ አይተርጉሙት፡ በእርግጥ በሕጋዊ መንገድ የተመረጡ ቢሆኑ ኑሮ፣እንደዚሁም ከልብም ለተወሰኑ ሳይሆን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ለምጣኔ ሀብት መቀየር፣ለጤና እንክብካቤ፣ለትምህርት፣ ለንጹህ ውሃ፣ ለግብርና ልማት፣ለቴክኒዎሎጅ ለውጥ እና ለመጠለያ መሻሻል ቢነሱ የሀገራችን መሪ አፍሪካን ሲወክሉ ሁላችንም ለማየት በወደድን ነበር። ምንም እጥረት እንኳን ቢፈጠር ያላድልወ በአግባቡ ቢከፋፈል ህዝብ ደስተኛ በሆነ ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ ለመሆኑ እርሰወ ባያጋንኑት ኖሮ የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት በ14% ቢመነደግ ማን ነው የማይደሰት? ነገር ግን የለየለት ውሸት? በተመሳሳይ ሁኔታ እርሰወ የራሰወትን የከባቢ አየር ይዞታ ደብቀው የአለማቀፉን ማህበረሰብ ባያታልሉ ኑሮ እርሰወ በኮፐንሀገን መወከለወት የማያስደንቀው ማን ኢትዮጵያዊ አለ? ጉዳዩ ግን እርሰወ ታላቁ የኢትዮጵያ አንድነት አፍራሽ ሆነው እንዴት ለተባበሩት አፍሪካ ተወካይ ሊሆኑ ይችላሉ? የእርሰወ የጎሳ ፖለቲካና የብሄረሰቦች ጥላቻ ጎሳወችን፣ ሀገሪቱን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን

ብሎም ቤተሰቦች፣ማህበረሰቦችን፣የሀይማኖት የሲቪል ተቋማትን፣ ሳይቀሩ ከፋፈሏቸው። ይህም የብሄረሰቦችን ግጭት የሚጭር ሁኔታ ፈጠረ፡ ይህ "ከፋፍለህ ግዛው" መርህ ለተወሰነም ጊዜ ቢሆን በስልጣን ሊያቆየወት ቻለ።

ጠቅላይ ሚኒስትር!

ኢትዮጵያዊያን አገዛዝወ ከእውነት በራቀ ቅኝት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ያውቃሉ። በኢትዮጵያ መኖር አስጠሊ ሆኗል። በዚህም የተነሳ ብዛት ያለው ሕዝብ አብላጫው ወጣቶች የሚበዙበት ሀገር እየለቀቁ መሰደድ ላይ ናቸው። ባገር ቤት የቀረውም ልክ ቅድመ አያቶቻችን ለምእተ አመታት እንደኖሩት አይነት በህይወት ውጣ ውረድ የሞት ሽረት ላይ ነው። በተቃራኒው ለማስመሰል በራሰወት የጎሳ ክልል አምስት ዩኒቨርስቲወች፣በርካታ ጥሩ ሆስፒታሎች፣ የንግድ ተቋማት ፣አሁን ደግሞ 2.5 ሚሊዮን ዶላር ወጭ የወጣቶች ማእከል ለማገንባት እቅድ ይዘዋል።
የኢትዮጵያን የተጠራቀመ ገንዝብና ሀብት ከሌላው ክልል እያጋዙ የአካባቢውን ህዝብ እየደለሉ ነው። ከጠቅላላው ሕዝብ ስሌት ሲሰላ ኢምንት ለሆነ አካባቢ ልዩ ጥቅም ለመስጠት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሳይቀር ሥራና የንግድ መመቻቸት ይደረጋል። በዚህ አይነት የተወላገደ አሰራር የብዙሀን ህይወት ሰቆቃ ውስጥ እየጨመሩ ህይወት ክብዷቸው ምንድን ነው ከነሱ የሚጠብቁት? እንደዚህ ነው መሪ መሆን ያለበት?

በአባትነተወ ከልጆቸወ አንዱ እንዲህ አይነት አድልወ ቢደርስበት ምን ይሰማወታል? ሁልጊዜ የአንድ ጎሳ አድልወ አለመረጋጋትን፣ጥላቻን ይፈጥራል። አሁን ገባወት? ልጆች ፣የልጅ ልጆች እና ወራሹ ትውልድ የቀጣዩ የብጥብጥ ኡደት ወራሾች እንዳይሆኑ አሁኑኑ ተጽኖውን ያንሱ?

"አዲሲቷ ኢትዮጵያ" "ሰብአዊነት ከጎሳ በፊት" ይቅደም የሚለውን መርህ በማራመድ ነጻነትን ለሁሉም የሚያጎለምስ እንድትሆን እንፈልጋለን ምክንያቱም "ሁላችንም ነጻ ካልሆን ማንም ነጻ ሊሆን አይችልም" ይህ የእርሰወን ልጆችና የልጅ ልጆች ጨምሮ ሁላችንም በተግባር መዋል አለበት።

አቶ ጠቅላይ ሚኒስትር! እራሰወትን በሌሎች ችግር ተክተው እንዲመለከቱት እንፈልጋለን።

- ምን አልባትም ኤች አይቪ የያዘው አንድ ወታደር ልጀወትን ቢደፍራት ምህረት ያደርጉለታል? በተመሳሳይ አይነት ችግር የወደቁ ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ሴቶችንስ?
- ወንዱ ወይም ሴቷ ልጀወት ተገዶ ወይም ተገዳ ወደ ሱማሊያ ቢሄዱና ቢሞቱ ምን ይሰማወታል? ምክንያቱም እርሰወ ሽብርተኝነትን መዋጋት "ስለፈለጉ" ብዙ ኢትዮጵያዊያንን አስገድደው ወደ ሱማሊያ አዝምተው አስጨርሰዋል። እርሰወ አልካይዳ መኖርን እንዳጋነኑት ባይሆንም የእርሰወ ጣልቃ ገብነት ግን ሁኔታውን አባባሰው፣እንጂ አላሻሻለውም፣
- ልጆቸወ በየሁለት ቀኑ ብቻ ቢበሉ ምን ይሰማወታል? ወይም ሁኔታው ተባብሶ ሁሉም በረሀብ ቢያልቁ? ምክንያቱም መንግስት የሚሰጠውን እርዳታ እሱን ለሚደግፉ ብቻ እንዲሰጥ እያደረገ ነው። በተቃራኒው ተቀናቃኝ ባሉበት የምግብ እደላውን በመዝጋት መላ ህብረተሰብ የረሀብ ሰለባ እንዲሆን ጭካኔ የተመላበት ተግባር እየተካሄደ ነው።
- መሬቱን የተወሰኑ የውጭ ሰወች ስለፈለጉት አዛውንት ወላጆቸወ ከቦታቸው ቢፈናቀሉ ምን ይሰማወታል?
- በተወለደችበት ብሄረሰብ አባላት በተፈጸመ ተግባር ቂም የያዘ ወታደር የትዳር ጓደኛወን ቢገልብወት ምን ይሰማወታል?

- አደገኛ የሆነ በሽታ ቢይዘወ ሙሉ በሙሉ በሀገረወ የጤና ተቋማት አስተማማኝ እንዲሆኑ ያደርጋሉ ወይስ ልክ ባለፈው ለአስቸኳይ ህክምና በድቅድቅ ጨለማ ወደ ቤልጀም ብራስለስ እንደሄዱት አይነት ተግባር ይተማመናሉ? የዛሬ ሁለት አመት ገደማ የአለም የጤና ድርጅት ሰራተኛ በግሉ ብዙ የጤና ባለሙያወችና ዶክተሮች ከመንግስት በሚደርስባቸው ወከባና ጭቆና የተነሳ ሀገር ጥለው እየተሰደዱ ነው ብሎ ሲጠይቀወ በሰጡት ምላሽ ኢትዮጵያ ዶክተር አያስፈልጋትም ሲሉ መልስ መስጠተወ የሚታወስ ነው። ይህ ከሆነ ጠቅላይ ሚኒስትር ይህ በእርሰወ ላይ ተፈጻሚነት እንዴት አይኖረውም?

ሚስተር ጠቅላይ ሚኒስትር!

ለመሆኑ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያዊያን በእርሰወ ላይ ያላቸውን ጥልቅ ብስጭት እየጨመረ መምጣቱን በውል ያውቁታልን? በአጣብቂኝ ውስጥ ነው ያሉት።ምክንያቱም ብስጭት በጨመረ ቁጥር አገዛዘወም ጭቆናውን እያጠበቀ ሲመጣ የህዝቡ መነሳሳት ደግሞ እያጋጋመው ነው። እውነት ለመናገር ከእንዲህ አይነቱ መረጃ የራቁ ይመስለናል ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት ትክክለኛ መረጃ የመቀበል ፍላጎት የለወትም።ሆኖም በግልጽ ለመናገር በእንዲህ አይነት ስርአት ኢትዮጵያዊያን የሚያጡት ነገር ኢምንት እየሆነ ነው።ማን ያውቃል ምን እንደሚፈጠር፤ የምጣኔ ሀብቱ አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል፤ጭቆናዊ አገዛዘወ ይበልጥ እየከፋ ነው፤ የኢትዮጵያን ቋሚ ንብረት ለሌሎች እየሸጡ ነው። ምርጫ እየተቃረበ ቢሆንም የፖለቲካው ምህዳር ለተቃዋሚወች በጣም የጠበበ ነው። መለስ የግለወን ደህንነት ለመጠበቅ ሲሉ ለትግራይ አድልዎ በማድረግ ላይ ነወት፤ ይህን የሚያደርጉት ለክልሉ ተወላጆች አስበው ሳይሆን እርቃኑን ለቀረ አገዛዘወ ሊያባብሉበት እንጂ የመጀመሪያውን የድርጅተወን ሰቆቃ የተጋፈጠው ይህ ህዝብ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው። ይህ ነው እንግዲህ መደለል፣ማስፈራራት አልያም ማግለል። የአንድ ፓርቲ ቁጥጥር በማድረግና "ጠላት ብለው" የመደቧቸውን በማፈን ከመምህረወ መንግስቱ ኃይለማርም አሰራር ጋር አንድ ደረጃ ያስቀደመወ።

አቶ ጠቅላይ ሚኒስትር!

ለትግራይ ብዙ ባደሉ ቁጥር የክልሉን ተወላጆች በብዛት በአንድ መስመር ለመያዝ በጣሩ ቁጥር በሌሎች ብሄረሰቦች ላይ የሚያሳድረው ቅሬታና መጠቃትን እየፈሩ በእርሰወ መንገድ እየተጓዙ ነው የሚባል ዘገባ ሲሰሙ በጣም ይወዱታል። በተለይ "የብሄረሰብ ግጭት" ተነሳ ሲባል እርሰወን ሊያስደስት ቢችል እንጅ የትግራይ ተወላጆች በጣም የሚሰጉበት ጉዳይ መሆኑን አላወቁትም። ምንም ይሁን ምን መረጋጋትን የሚፈልጉት ብዙ ናቸው።
እርሰወ በምርጫ 1997 ወቅት እንደተናገሩት ቅንጅት ካሸነፈ በኢትዮጵያ የሚደርሰው ጥፋት በሩዋንዳ ከተፈጸመው በላቀ መልኩ ነው በማለት ሽብር ነዙ፤ በህዝቡ ላይ ፍራቻ ለመፍጠር የቅንጅት ተመራጮችን "በዘር ማጥፋት ሙከራ" ወነጀሉ። ሀቁ ግን እርሰወ የፈጠሩት ጉዳይ ቡድንና እንደ በረከት ስምኦን ያሉ ተባባሪዎች ያከናወናችሁት ጥፋት ነው። የዚሁ ጥፋት ፈጻሚወች አሁን በሀገሪቱ እንደልባቸው ይኖራሉ፣ ልቅ ወጥተዋል። ነገር ግን ለፈጸሙት ወንጀል በሃላፊነት ከመጠየቅ አያማልጡም።

በተቃራኒው ሀገራችን ወደ አለመረጋጋትና በአመፅ ከመታመሷ በፊት የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄ /አኢትን/ በኢትዮጵያዊያን እህቶችና ወንድሞች መካከል እርቀ ሰላም እንዲወርድ አበክሮ ይሰራል። ሂደቱም እያንዳዳችን ለመገናኘት የምንፈላለግበት ወቅት ነው መደረሱንም አበክረን መግለጽ እንፈልጋለን። በቅርቡ በአሜሪካ ከተማ ዋሽግተን ዲሲ በኢትዮጵያና በአፍሪካ የዘር ማጥፋትንና አባገነንነትን የተቃወመ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የአኢትን አባላት ተገኝተን ነበር።

በዚህ ወቅት የምንጓዝበት ታክሲ ነጅ ከትግራይ የመጣና የሕወሃት ቀደምት አባል እንደነበርና ድርጅቱ የተነሳለትን አላማ የስልትና ታክቲኩም ስላልጣመው ትቶ መውጣቱን ነገረን።አሁን ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር እንደማይገናኝ እራሱን አግልሎ እንደሚኖር፣ ሆኖም ግን ሀገሩን ወዳድ መሆኑንና በተፈጸመው እንደሚጸጸት ሳይደብቅ አብራራልን። ባደረግነውም አጭር ውይይት የመርህ ሰው መሆኑና ግልጽ ሀሳብ ያለው  ሁኖ ነው የተረዳነው፣በመጨረሻም በሰልፍ እንዲሳተፍ ጋበዝነው ቤተሰቦቹን ይዞ ተገኘ።

ሌላው ከትግራይ የመጣች ሴት የነገረችን ታሪክ ባጭሩ እነሆ፣" ትግራይ በመወለዴ ብቻ በደርግ ዘመን ገጣይ ተብዬ መገለል ደርሶብኝ ነበር።አሁን ደግሞ ህወሃት የደርግ አቀንቃኝ ይለኛል።ይህ አይነት ጥላቻ በደርግ እንደነበረው አዙሪት ውስጥ ነው ያለው ደርግ በጣም የጀርባ ውጋት ነበር በትግሬዎች ላይ ጥላቻ ነበረው። በወያኔና በትግራይ መካከል ልዩነት ሳያደርጉ፣ አሁንም ወያኔ ከነገሰ በኃላ ተመሳሳይ ነው፤ አማራን እንድንጠላ ይሰብኩናል፣ አማራዎች ስልጣንና ሀብት በአንድ ላይ ይዘው ይጨቁኑን እንደነበር በየቀኑ በፀረ-አማራ ቅስቀሳ አምሮአችን አበላሽተውታል።"

"ወያኔ ስልጣን በጨበጠ ወቅት ሁላችንም ትግሬወች ከእርሱ ጎን እንድንሰለፍ ጠብቀው ነበር። ይህን ያላደረጉ "የውጭ" ተብለን እንመደባለን። የመጀመሪያው የወያኔ ጥቃት ሰለባ ግን የትግራይ ህዝብ ነው። ህወሀትን ባለመደገፍ የተገደለ፣የተገረፈና የተጋዘ የትግራይ ተወላጅ ነው።ህወሃት ስልጣን ሲይዝ ከእርሱ ጋር መስራት ቀጥየ ነበር።ነገር ግን በህግ አይን ስመዝነው ሚዛን ሊደፋ አልቻለም በተጨማሪ ድርጅቱ እኔን "ጥሩ ትግሬ" አይደለችም ወደማለት መሸጋገራቸውን ተረዳሁ፣ በዚህ የተነሳ ሀገሩን ትቼ ወጣሁ። አሁን ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር ችግር የለብኝም፣ ሲያገኙኝ ቆም ብለው ያወሩኛል፣ ያጫውቱኛል። ትግሬወች ይህ መንግስት ለትግራይ መጥፎ መሆኑን ያውቃሉ። ብዙዎች ምርጫውንና የብርቱካንን መታሰር አውግዘዋል።ጥሩ ሰላም ፈላጊና ኢትዮጵያ ነጻነት እንዲኖር የሚፈልጉ ትግሬዎች ቁጥር የትዬ ለሌ ነው። በኢትዮጵያም ነጻነት እንዲኖር የሚፈልጉ የአኢትን ከወያኔና ከትግራይ ደጋፊ የለውም ብለው እንዳይገምቱ ።ንቅናኤው ከሁሉም ህብረተሰብ ድጋፍ አለው። የእናንተ መልክት "ሁላችንም ነጻ ካልወጣን ማናችንም ነጻ አይደለንም" የሚለው መርህ ወያኔን ጨምሮ ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን የሚያደርስ ነው። ምክንያቱም የወያኔ ደጋፊዎች ነጻ አይደሉም "ከብሄረሰብ በፊት ሰብአዊነት"ይህም ለእኛ ለትግሬዎችና ወያኔም ሰው በመሆኑ ይደርሰዋል። ለኢትዮጵያዊያን ንገሯቸው ትግሬዎችን በመደዳ ከወያኔ ጋር መፈረጅ የትግራይ ተወላጆችን ከወያኔ ጋር ይበልጥ ሙጥኝ እንዲሉ ያድረጋል እንጂ ኢትዮጵያን አይጠቅምም ምክንያቱም ትግሬዎች የመውጫ በር ይዘጋባቸዋል።

ትግሬወችን በስርአት ቀረቧቸው በአስፈላጊው ሁኔታ ከእኛ ጋር አብረው እንዲሰሩ ተቋቋሚቻቸው የአኢትን መርህ በሁሉም ኢትዮጵያን እንዲደርሳቸው ትኩረት ሊደረግ ይገባል። አገዛዙን ሙጥኝ ብሎ የያዘውን አስተሳሰብ መፈረካከስ ከተፈለ ይህ ዋናው ብልሃት ነው። በእርግጥ የተሻለች ኢትዮጵያን ለማየት የምንሻ ከሆነ ይህ መርህ በተገቢው ሊተኮርበት ይገባል"

ስትል ነበር አስተያየቷን የሰጠችን። ልክ እንደዚች ሴት አቶ ስዬ አብርሃ የብሄረሰቡ አባላት መካከል አንዳንዶች ከፍተኛ ግፊት የሚያደርጉባቸው አሉ።ለአብነት ያህል መንግስት በሚመራው የዋልታ ኢንፎርሜሽን ወይብ ሳይት ተጽፎ ለአንባቢ በግልጽ የወጣውን እንመልከት "ኩሩው የትግራይ ልጅ ስዬ አብርሃ ለምንድን ነው  ትግራይ በቀል ከሆነው አረና ላይ ፊቱን ያዞረው እና በ1997 ዓ.ም ምርጫ በትግሬወች ላይ ከዘመተ ድርጅት ጋር መቀላቀሉ?" የሚለውን ተመልከቱ። በትግሬወች መካከል ይህ አይነት ስሜት እንዲኖር መደረጉ የእርሰወ የተግባር ውጤት ነው። ይህ ሁሉ ሁኖ እርሰወና የእርሰወ ጋሻ ጃግሬወች አይደላችሁምን በትግራይ በቀሉ አረና ትግራይ ላይ ፊታችሁን ያዞራችሁት? ለተፈጠረውም

ጥላቻ ቢሆን ተጠያቂው እርሰወ ነወት። ከላይ ሀሳቧን የገልለጸችው ሴት አይነት ብዙ ታሪካቸውን ያልዘረዘርነው የእርሰወ ስልጣን መቆናጠጫ ነበሩ። የስዬ አብርሃ ፈለግና እርምጃ ተከትለው በርካታ የትግራይ ተወላጆች አዲሲቱን ኢትዮጵያ ወደ መገንባት "ጎራ" እንደሚቀላቀሉ እና ለአገዛዘወ ትልቅ  ስጋት እንደሚፈጥር ይተወቃል። የትግራይ ህዝብ ወንድሞቻችናን እህቶቻችን ናቸው። እናም የንቅናቄአችን አባላት ትልቁ ትኩረታችን የእርሰወ አመራር የፈጠረውን የጥላቻ መንፈስ በማስወገድ በሁሉም የሀገሪቱ ህብረተሰብ መካከል እርቀ ሰላም እንዲወርድ መጣር ነው። ወያኔ በሚቆጣጠረው የአንድ ፓርቲ መንግሥት የተፈጠረውን የጥላቻና የጎሳ ውዝግብ አብዛኛው የትግራይ ተወላጅ አይደግፈውም ።እርሰወም ሆኑ በእርሰወ ዙሪያ ያሉ ሁሉ ይህንን ቆራጥ አቋም እንድትወስዱ እንጠይቃለን?

ጠቅላይ ሚኒስትር

በእኛ በኩል አሁን እየነጎዱ ያሉበትን የአሰራር ጎዳና ይቀይራሉ የሚል ምክንያት የለንም። ነገር ግን ሁሉ እርምጃወ ለራሰወ ሕልውና እና ጥቅም ብቻ ነው ሁኖም ይህ ጉዞ ግን በረጅሙ ሲመዘን ትግራይን ጨምሮ ለኢትዮጵያ ህዝብ በጣም ግልጽ የሆነ አደጋ አለበት። በመሆኑም ይበልጥ ግልጽ ለመሆን እኛ የአኢትን አባላት ስለእርሰወና አገዛዘወ ብዙ አፍራሽ ነገር እንላለን ይህን ስንገልጽ በዚህ ደብዳቤ ብቻ አይደለም በጽሁፍ፣በንግግር፣በደብዳቤወች፣ በሰላማዊ ሰልፎች እንደዚሁም ወስጥ ለውስጥ ከኢትዮጵያዊያንና  ከውጭ ሰወችና ድርጅቶች ማለት ከአለማቀፍ የወንጀለኞች ችሎት፣ከአሜሪካ ምክር ቤት፣ከእንግሊዝ ፓርላማ፣ ከየሀገራቱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችና የመንግስታት ባለስልጣናት፣ወሳኝ የፖሊሲ ሰጭወጭ እና ከመገናኛ ብዙሀን ጋር እንጻጻፋለን። ይህን ስናከናውን ግን በመረጃ ላይ ተመስርተን መሆኑን ልናረጋግጥለወ እንወዳለን። በማንኛውም ጉዳይ ስህተት ከተገኘብን ይቅርታ እየጠየቅን ለማረም ዝግጁ መሆናችንን እናረጋግጣለን ።

ጠቅላይ ሚኒስትር

እንደሚያውቁት የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄ /አኢትን/ የተቃዋሚ ቡድን አይደለም።በአንጻሩ መንግስተወ በህዝቡ ላይ የሚያደርስበትን  የመብት ጥሰት መከላከልና ማጋለጥ፣ ስህተት የፈጸሙ እንዲታረሙ፣ የማይታረሙ ከሆኑ በህግ እንዲጠየቁ የማድረግ ሂደት ተግባራዊ እንዲሆን መስራት ነው። ስለሆነም ዋናው ግባችን የእርሰወን ስልጣን መንጠቅ አይደለም። ነገር ግን ከሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ከአምባገነን አሰራር፣ ከጎሳ ጥላቻ አገዛዘወ እንዲታርም እውነታውን ለህዝብ ማሳየት ነው። አገዛዘወ የዘር ማጥፋት አካሂዷል፣ በሰብአዊነት ላይ ወንጀል ፈጽሟል፣ አሁንም እንደቀጠለነው። በመከላከያ ጦሩ በታህሳስ ወር 1996 በአኝዋክ ላይ የተጀመረው ዘር ማጥፋት ያባራው ሰራዊቱ ፊቱን  ወደ ኦጋዴንና ሶማሊያ ሲያዞር ነው። እርሰወ በሚጋባ እንደሚያውቁት በፌደራሉ የአካባቢ ጉዳዮች መስሪያ ቤት አዝማችነት በአኝዋክ፣ በኦጋዴ፣ በአፋር፣ በኦሮሚያ ከዚህም በተጨማሪ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ይህንን ጥፋት ያስፈጸሙት አገዛዘወን ስለተቃወሙ ብቻ ነው። አኝዋክን በተመለከተ ዘመቻው የነዳጅ ዘይት ሀብት ጥቅም የጨመረ ነው። ልክ የኦጋዴን ነዳጅና ዘይት ፍለጋ አይነት ማለት ነው።ብዙ ኢትዮጵያዊያን በነዳጅ ፍለጋው  ተቃውሞ የላቸውም ነገር ግን የአካባቢው ነዋሪወችን የደህንነት ዋስትና ያስጠበቀና በሀብቱም ተገቢ የሆነ ተጠቃሚነትን ሚዛን ውስጥ ያስገባ ተግባርና ውል እንዲኖር ያስፈልጋል። ጉዳዩ ግን ይህ አይደለም የእኛ ስጋት የእርሰወ አመራር "ካገኘሁት ምንም ይሁን" የሚል  ለእርሰወ ጠቀሜታ ብቻ በሚያመች መንገድ በመላ ሀገሪቱ የዘረጋው የሀብት ማጋበስ ስምምነት ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር! በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ከቀደምት መሪዎች በተለየ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ደህንነት ጣሱ በተቃራኒው የእርሰወ የሀገር ክህደት እውነተኛው

የኢትዮጵያ ልጆች ሀገራቸውን አመራር ሲይዙ ሀቁ ይወጣል። ሆኖም ከብዙ አመት የማፍረስ ተግባር በኃላ መልሶ መገንባት ቀላል ሥራ እንደማይሆን ግልጽ ነው። ጊዜው እየቀደመ በመሆኑ የእርሰወን የየቀን ማፍረስ ተግባር እየተመለከተ ማን አርፎ ይቀመጣል? እኛ የአኢትን አባላት ይህን የምንለው ለሽዎች ብቻ ወክለን አይደለም። በሚሊዮን ለሚቆጠሩ በዚህ መርህ የሚያምኑትን የወከለ ነው። ብዙዎችም የዚህ ሀሳብ ተጋሪዎች በሀገር ቤት ውስጥ ናቸው። ያሉት በአገዛዝወ ዙሪያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሳይቀር ንቅናቄአችን ከፍተኛ ደጋፊዎች አሉት። የንቅናቄው አመሰራረትም መላው ኢትዮጵያ በሚወክሉ ወገኖች ነው የተዋቀረው። ለእኛ በሀገራችን ያለው ልዩነት ሀብተችን ነው። የኢትዮጵያ ማህበረሰብ በተፈጥሮ ተጠብቀው የኖሩ እንጂ እርሰወ እንዳሉት የትግራይ ብሄረሰብ ብቻ “ወርቅ” እና “የተመረጠው” ነው። ከሚሉት አባባልወ በተቃራኒው የቆመ እምነት ነው።እርሰወ ተሳስተዋል በአምላክ አይን ሁላችንም “ወርቆች” እና “ የተመረጥን” ነን። ቢያንስ ይህን እንዳይረሱ።

ጠቅላይ ሚኒስትር

ምንም ነገር ቢሰሩም እርሰወንና የከበቡወትን ሰዎች የምናየው ሁላችሁም አምላክ በአምሳሉ በቀዳሚ ከፈጠራቸው ሰብአዊ ፍጥሮች ጨምረን ነው።እንደ ኢትዮጵያ ያለ 80 ሚሊዮን ህዝብ መሪ በመሆነወ ይህ ምርጫ በህዝቡ ላይ ታላቅ ተጽእኖ አለው።ብቸኛው የችግር መፍትሄ ጥሩ የሆነ ውሳኔ መስጠት ብቻ ነው። ይህ ምርጫ ለሀገሩቱም ጭምር ጠቃሚ ነው። ብለን እናምናለን ይህን ሀሳብ ቢረዱት በጣም ጥሩ ነው። ነገር ግን አሁን ባለው ሕግ ተብዬ ይዞታ አይነውን ጨፍነው ከቀጠሉ ከባድ ስሁተት ነው። በጣም ከመዘግየቱ በፊት ለኢትዮጵያ የሚያደርጉትን ጥሩ ነገር ያሰላስሉ ያስቡበት አሁን ባለው ለመቀጠል ከፈለጉ የራሳችን እርምጃ በኢትዮጵያ የፍትህ ስርአት ወይም በአለማቀፍ ወንጀለኞች ችሎት አማካኝነት ከህግ ፊት ቀርበው እንዲዳኙ ለማስቻል ትግላችን ይቀጥላል። በኮፐንሀገን አሁንም አርማችን አንስተን እንጠብቀወታለን፣ ኢትዮጵያዊያንን በጋዜጣዊ መግለጫ እንዲጋፈጧቸው እየጋበዝን ግብዛችን ለእርሰወ እንጂ ለወኪለወ አለመሆኑንም ይረዱልን።

አቶ ጠቅላይ ሚኒስትር

የማይታሰበውን ይስሩ ህዝቡ በእርሰወ ተማሯል። ምሬቱም ከበቂ በላይ ነው። ለሁሉም ጥቅም ሲባል የእርሰወ እርምጃ ለውጥ ያመጣል።ለቂም በቀል የአሰፈሰሩትንም ሳይቀር ያቀዘቅዛል። ብዙ ነገር ሊሰሩ ይችላሉ ነገር ግን አሁንም እንደሚጠበቀው የኢትዮጵያን ህዝብ በኃይል መግዛት ከመረጡ ከገጠመወት ችግር መውጫ እንደሌለወ ይወቁ።
ኢትዮጵያውያንም ለፈጸሙት ወንጀል ተጠያቂ ያደርጉዎታል። በእርሰወ ዙሪያ ያሉና ለኢትዮጵያ ውድቀት አስተዋጾ ያደረጉ በነቂስ ተለይተው ይታወቃሉ በህግ ፊትም ተጠያቂ ይሆናሉ። ነገር ግን ያተረፉት መጥፎ ስምና ዝና ለመቀየር የሚከተሉትን እርምጃ እንዲወስዱ ሀሳብ እናቀርባለን፤

1. ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳን እና በአስር ሽህ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞችን እንዲፈቱ፣
2. ነጻና ገለልተኛ የምርጫ አስፈጻሚ በሀገሪቱ እንዲቋቋም፣
3. ሕዝቡን የሚጨቁኑበትን ኃይል ተጠቅመው የፖለቲካውን የተሳትፎ ደረጃ ለማስፋት እርምጃ እንዲወስዱ፣
4. ነጻ የመገናኛ ብዙሀን እንዲኖር እንዲፈቅዱ፣
5. ስልጣን በፈቃደወ ያስረክቡ፣

6. አግባብ የሆነ ነጻና ግልጽ ምርጫ እንዲካሄድ ተጨባጭ እርምጃ ይውሰዱ፣

7. የሕግ ስርአቱን መቆጣጠሩን ያቁሙ! የፍርድ ቤቶችን ነጻነት ያክብሩ፣

8. የወታደራዊና የደህንነት ተቋማቱ አሰራር መርህ በብቃት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን፣ በተጨማሪ ተቋማቱ ለሁሉም ብሄረሰቦች ከፍተኛ ሃላፊነትን ጨምሮ ያሉ ቦታዎች ክፍት እንዲሆኑ፣

9. ሰብአዊ መብትን መጣስ ያቆሙ ወንጀለኞችንም ለፍርድ ያቅርቡ፣

10. እውነቱን ተናግረው የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ ይጠይቁ፣

11. ብሄራዊ እርቀ ሰላም እንዲወርድ ሁኔታወችን እንዲያመቻቹ እንጠይቃለን፣

ጠቅላይ ሚኒስትር

በአህጉራችን ታሪክ ሲጀምሩ በተሳሳተ ጎዳና የተጓዙ ሲጨርሱ ግን በመልካም ያጠናቀቁ የመጀመሪያው አፍሪካዊ መሪ ለመባል የሚያስችልን መሰረታዊ ለውጥ ያለው ሥራ ላይ እንዲያተኩሩ፣ ይህን መሰል እድል አሁን ካመለጠወ ግን ምን ጊዜም ቢሆን አያገኙትም በመሆኑም ያለፈ ጉድፍ ማራገፊያው ወቅትና ለኢትዮጵያ የወደፊት የተሻለ ግንባታ እራሰወትን የሚያቀርቡበት አጋጣሚ ይህ ወቅት ነው።መልሰወትን እንጠብቃለን።

ከሰላምታ ጋር

የአኢትን ሥራ አስፈጻሚ አባላት

ለማነጋገር ኦባንግ ሜቶ የስራ አስፈጻሚ ሰብሳቢን ያነጋግሩ
PO. Box.50561
Arlington. VA 22205
Email: obang@solidaritymovement.org
Website www.solidaritymovement.org

ይህ ደብዳቤ ከዚህ በታች ለተዘረዘርሩት ሁሉ ግልባጭ ተልኳል፣
-ለፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ
-ለምክትል ፕሬዚዳንት ጆሴፍ ባይደን
-ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሂለሪ ክሊንተን
ለመከላከያ ሚኒስትር ሮበርት ጌት
-ለብሄራዊ ደህንነት አማካሪ ጀነራል ጀምስ ጆን
-ለምክር ቤት አባልና የህግ መወሰኛው ምክር ቤት የውጭ ጉዳይ ሊቀመንበር ጆን ኬሪ
-ለምክር ቤትና የህግ መወሰኛው የውጭ ኮሚቴ አባል ሪቻርድ ሉገር
--ለምክር ቤት አባልና የአፍሪካ ጉዳዮች ሊቀመንበር ሩዜል ፊንጎልድ
--ለምክር ቤት አባልና ለውጭ ጉዳይ መምሪያ ሊቀመንበር ፓትሪክ ሌሂ
-ለምክር ቤት አባልና በውጭ ግንኙነት የአለማቀል ልማት ሊቀመንበር ሮበርት መነንደዝ
-ለተወካዮች ምህር ቤት አባልና ለአፍሪካ አህጉር የጤና ንዑስ ኮሚቴ ሊቀመንበር ዶናል በይን
-ለካናዳ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሌወራንስ ካኖን

-ለእንግሊዝ የውጭ የጋራ ጉዳዮች ሚኒስትር ዴቪድ ሚሊባንድ
-ለጀርመን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጉይዶ ዌስተርዌየል
-ለፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በርናርድ ኮቸር
-ለሲዊድን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ካርል ቢልድት
-ለጃፓን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ካሱያ ኦካዳ
-ለአውሮፓ ህብረት የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር ገብሬል አልበርቲኒ
-በአለም ለሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲወች ሁሉ
-ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ ለሆኑ ላጋሽ ሀገራት ኤምባሲወች
-ለዋና ዋና የመገናኛ ብዙሀን.